# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

## አንደኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት

# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር
# አንደኛ ክፍል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ዓለም አቀፍ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

# ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ ........................................................... | |
| አጠቃላይ የትምህርቱ ዓላማ ........................................ | |
| ምዕራፍ አንድ ....................................................... | ፩ |
| ቤተ ክርስቲያን ...................................................... | ፩ |
| ፩.፩ ነጠላ በትዕምርተ መስቀል አጣፍቶ መልበስ ...... | ፫ |
| ፩.፪ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት ስንሳለም ምን እንላለን?................................................ | ፭ |
| ፩.፫ ስግደት በቤተ ክርስቲያን ................................ | ፭ |
| ፩.፬ በቤተ ክርስቲያን መደረግ ያለበትና የሌለበት ድርጊቶች ................................................... | ፯ |
| ፩.፭ ቅዱሳት ሥዕላትን መሳለም.............................. | ፯ |
| ፩.፮ የካህናትን መስቀል መሳለም .......................... | ፰ |
| ምዕራፍ ሁለት ...................................................... | ፲፩ |
| መታዘዝ እና ጥሩ ልጅ መሆን ..................................... | ፲፩ |
| ፪.፩ ለሰው ሁሉ መታዘዝ .................................... | ፲፪ |
| ፪.፪ በመታዘዝ የሚገኝ በረከት .............................. | ፲፩ |
| ፪.፫ ለወላጆች ስለመታዘዝ ................................... | ፲፫ |
| ፪.፬ ጥሩ ልጅ መሆን ......................................... | ፲፯ |
| ምዕራፍ ሦስት ....................................................... | ፲፱ |
| ጓደኝነት ............................................................... | ፲፱ |

# ማውጫ

አርእስት ገጽ


፫.፩ ሰውን ሁሉ ስለመውደድ ................................ ፳

፫.፪ ጥሩ ጓደኝነት ............................................ ፳፩

፫.፫ መጥፎ ጓደኝነት ............................................ ፳፪

ምዕራፍ አራት ........................................................ ፳፭

ጸሎት ................................................................ ፳፭

፬.፩ ጸሎት ምንድነው?........................................... ፳፮

፬.፪ እንዴት እንጸልይ ......................................... ፳፯

፬.፫ አባታችን ሆይ እና እመቤታችን ሆይ .............. ፳፰

፬.፬ ስለምን እንደምንጸልይ .................................. ፴

፬.፭ የት እንደምንጸልይ ....................................... ፴

ምዕራፍ አምስት .................................................... ፴፫

መዝሙር ............................................................... ፴፫

፭.፩ የመዝሙር ጥቅም ......................................... ፴፬

፭.፪ መዝሙር ስለመዘመር ..................................... ፴፬

፭.፫ እንዴት እንዘምር? ........................................ ፴፭

# መግቢያ

በቤተ ክርስቲያናችን ከሚሰጡ መንፈሳዊ ትምህርቶች መካከል አንዱ ክርስቲያናዊ ስነ ምግባር ነው፡፡ በሃይማኖት ትምህርት ውስጥ እንደምንማረው ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገባው እግዚአብሔርን አምኖ እና መልካም ሥራ ሠርቶ ነው፡፡ መልካም ሥራ ሊሠራ የሚችለው ደግሞ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን በደንብ ሲያውቅ እና ሲገነዘብ ነው፡፡ የዚህ ትምህርት ጥቅም በእምነት ውስጥ ያሉ የቤተክርስቲያኒቱን ልጆች መልካም ስነ ምግባርን አጣምረው ይዘው ለእግዚአብሔር መንግሥት ዝግጁ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

# አጠቃላይ የትምህርቱ ዓላማ

## ተማሪዎች ይህን ትምህርት ሲያጠናቅቁ፡

፩. ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ ማድረግ ስለሚገባቸው ተግባር ይገነዘባሉ፡፡

፪. የመታዘዝን መልካምነት ይረዳሉ፡፡

፫. ጥሩና መጥፎ ጓደኝነትን ይለያሉ፡፡

፬. ጸሎት መጸለይ እንደሚገባ ይረዳሉ፡፡

፭. መዝሙር የመዘመርን አስፈላጊነት ይረዳሉ፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# ቤተ ክርስቲያን

## የምዕራፉ ዓላማ

ልጆች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ፦

- ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ ማድረግ የሚገባቸውንና ማድረግ የማይገባቸውን ተግባራት ይለያሉ፡፡
- ቤተክርስቲያን ሲመጡ ነጠላ አጣፍተው መልበስን ይለማመዳሉ፡፡
- ቤተ ክርስቲያን የሚመጡበትን ዓላማ ያብራራሉ፡፡
- ወደቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ምን እያሉ እንደሚገቡ ያውቃሉ፡፡
- ቅዱሳት ስእላትን እና መስቀል መሳለም እንደሚገባቸው በደንብ ይገነዘባሉ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- ቤተክርስቲያን፦ የክርስቲያኖች ቤት የጸሎት ቤት ማለት ነው፡፡
- ማማተብ፦ በሥላሴ ስም በመስቀል አምሳያ ሰውነታችንን መባረክ ማለት ነው፡፡

👉ልጆች በዛሬው ትምህርታችን ስለ ቤተ ክርስቲያን እንማራለን ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ምን ማድረግ እንዳለብንና ምን ማድረግ እንደሌለብን እግዚአብሔር ያስተምረናል፡፡

የማስጀመሪያ ጥያቄዎች ፡- ልጆች ስለ ቤተክርስቲያን ምን ታውቃላችሁ?
ለምን ቤተክርስቲያን ትመጣላችሁ?
ቤተ ክርስቲያን ስትመጡ (መጥታችሁ) ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ?
ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

👉ልጆች ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደሪያ ነች፡፡ ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን መላእክት የምትጠበቅ የጸሎት ቤት ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለምን እንደምትሄዱ ስትሄዱ ምን እንደምታደርጉ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



ሥዕል ፩.፩ ፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

👉ልጆች ቤተ ክርስቲያን የምንሄደው ለምን መሰላችሁ?

፩. ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት፤

፪. ምስጋና ለማድረስ፣ ቅዳሴ ለማስቀደስ፤

፫. ለመቊረብ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር እንመጣለን፤

፬. ከታመምን ለመዳን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንመጣለን፤

👉ልጆች ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ምን ምን ማድረግ አለብን?

## ፩.፩ ነጠላ በትዕምርተ መስቀል አጣፍቶ መልበስ

ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ ከምናደርጋቸው ነገሮች አንዱ ነጠላ በትዕምርተ መስቀል አጣፍቶ መልበስ ነው፡፡



ሥዕል ፩.፪ ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን

👉 ልጆች ከላይ ያለውን ሥዕል እያያችሁ የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ፡፡ ሁሉም ተመሳሳይ የሆነ ምን ለብሰዋል? ለምን? እንዴት ነው የለበሱት? እናንተስ እንደ እነርሱ መልበስ ትችላላችሁ?

## ልጆች ለምን ነጭ ነጠላ እንደምንለብስ ታውቃላችሁ?

- አዎ ምክንያቱ ነጭ ልብስ ለብሰው ጌታቸውን የሚከተሉትን የጻድቃንና ቅዱሳን መንገድ እና እምነትን ስለምንከተል ነው
- ምሳሌ ነው፡፡ ‹‹ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፡፡›› (የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ ፮ ከቁጥር ፱ እስከ ፲፮)
- ቅዱሳን መላእክት የጌታን ትንሣኤ ሲያበሥሩ የለበሱት ነጭ ነበር፡፡

በዚህ መሠረት ቅዱሳን አባቶቻችን ይህንን ሥርዓት አስቀምጠውልናል እኛም የአባቶቻችንን ትምህርት ተቀብለን ነጭ ነጠላ በትእምርተ መስቀል አጣፍተን እንለብሳለን፡፡



ሥዕል ፩.፫ ነጠላ አጣፍታ የለበሰች ልጅ

## ፩.፪ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግባት ስንሳለም ምን እንላለን?

- ልጆች የቤተ ክርስቲያን መግቢያ ላይ ሆነን ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ እንሰጣለን እጅ እንነሳለን።
- በትዕምርተ መስቀል እናማትባለን
- "ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት "ትርጉም የሰማያዊት ኢየሩሳሌም አምሳያ የሆንሽ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል።
- እንሰግድና መሬቱን ስመን ጫማችንን አውልቀን ወደ መቅደስ ውስጥ እንገባለን።

## ፩.፫ ስግደት በቤተ ክርስቲያን

ልጆች ቤተ ክርስቲያን ስንገባ ተሳልመን ሰግደን መሆን አለበት። ስንሰግድም እንዲህ ማለት ይገባናል።


- ለአብ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ የአምልኮት ስግደት።

ለአብ ምስጋና ይገባል ለወልድም ምስጋና ይገባል ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል እያልን (ሦስት ጊዜ)፤

- ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የጸጋ ስግደት እንሰግዳለን።

አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና ይገባል እያልን (አንድ ጊዜ)፤

- መድኃኔዓለም ለተሰቀለበት መስቀልም የጸጋ ስግደት እንሰግዳለን ዓለምን ለማዳን ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ ለተሰቀለበትም መስቀል ምስጋና ይገባል እያልን (አንድ ጊዜ)
- በተጨማሪም ለቅዱሳንም እንዲሁ የጸጋ ስግደትን እንሰግዳለን።



ሥዕል ፩.፬ ሕፃን ልጅ በቤተ ክርስቲያን ሲሰግድ

## ፩.፬ በቤተ ክርስቲያን መደረግ ያለበትና የሌለበት ድርጊቶች

- ልጆች ገና ከቤታችን ሳንነሳ ቤተክርስቲያን መምጣት ስናስብ ዝግጅት ማድረግ አለብን ልብሳችን ሰውነታችን ንጹሕ መሆን አለበት ንጹሕ ልብስ መልበስ አለብን፡፡

| መደረግ ያለበት | መደረግ የሌለበት |
|---|---|
| ሰዓት ሳናረፍድ ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት አለብን | በቤተክርስቲያን የማይረባ ወሬ ማውራት፣ ጮሆ መነጋገር የለብንም |
| ነጠላችንን በትዕምርተ መስቀል ለብሰን መገኘት አለብን | መሯሯጥ ፣የሌሎችን ሰላም የሚረብሽ ምንም አይነት ነገር ማድረግ የለብንም |
| በመንገድ ላይ ልብሳችንን ሳናቆሽሽ መምጣት አለብን፡፡ | ማልቀስ ወላጅን እንሂድ እያሉ ጸሎት ማቋረጥ የለብንም |

| መደረግ ያለበት | መደረግ የሌለበት |
|---|---|
| ግቢ ከገባን በኋላ ግቢውስጥ በሥርዓት መራመድ አለብን | ቤተመቅደሱ ውስጥ ምግብ መመገብ የለብንም |
| ለቅዳሴና የምንቆርብ ከሆነ ወደ ውስጥ ገብተን ማስቀደስ አለብን | መጫወት |
| ቤተመቅደሱ ጋር ሄደን ጸሎት አድርሰን ተሳልመን መግባት አለብን | መጣላት ወይም መሳደብ የለብንም |

ሰንጠረዥ ፩ በቤተ ክርስቲያን መደረግ ያለበትና የሌለበት ድርጊቶች

## ፩.፫ ቅዱሳት ሥዕላትን መሳለም

👉 በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ ቅዱሳት ሥዕላትን መሳለም አለብን፡፡.



ሥዕል ፩.፫ ሕፃን ልጅ ቅዱሳት ሥዕላትን ሲሳለም

## ፩.፮ የካህናትን መስቀል መሳለም

- አባቶቻችን ካህናትን በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በመንገድ ላይ ስናገኛቸው አባታችን ይባርኩን ብለን ቡራኬ መቀበል እና መስቀል መሳለም አለብን።



ሥዕል ፩.፮ መስቀል የሚሳለም ልጅ

### ተግባር

መምህሩ ለተማሪዎች በተግባር የሚያሳዩት

- ነጠላ በትዕምርተ መስቀል አጣፍቶ መልበስን ፣
- ለማማተብ እጅን በመስቀል ቅርጽ ማዘጋጀትን፣
- በአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ደጃፍ ከልጆቹ ጋር በመሆን በማማተብና፣
- በመስገድ ወደ ቅጥረ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደሚገቡ ማሳየትና ልጆቹም እንዲሁ እንዲያደርጉ ማስቻል ማለማመድ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

👉ተማሪዎች ከላይ የተዘረዘሩትን መንፈሳዊ ተግባራት በተማራችሁት መሠረት ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትመጡና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሆናችሁ ጊዜ ሁሉ ያለማቋረጥ እያደረጋችሁ ልትለማመዷቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም የሚቸግራችሁ እና ያልገባችሁን ነግሮች ደግሞ ከሚያስተምሯችሁ መምህራኖች እና ከቤተ ክርስቲያን አባቶች እንዲሁም ከቤተሰቦቻችሁ ጭምር በመጠየቅ ማወቅና መፈጸም ይኖርባችኋል፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

፩. ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ስናስብ ወንዶችም ሆነ ሴቶች ነጠላ መልበስ አለብን?

፪. ቤተ ክርስቲያን ስንሳለም በመጀመሪያ በስመ ሥላሴ ማማተብ አለብን?

፫. ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ወላጆቻችን እንጂ እኛ ልጆች መስግድ አይጠበቅብንም?

በ “ሀ” ስር የተዘረዘሩትን በ “ለ” ስር ካሉት ጋር ተስማሚያቸውን በመስመር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| ፩. ቤተክርስቲያን ስንሄድ የምንለብሰው | ሀ. መስቀል |
| ፪. ለቤተክርስቲያን ወይም ለመቤታችን የሚቀርብ ሰላምታ | ለ. ነጠላ |
| ፫. በካህናት እጅ የምንሳለመው | ሐ. ሰላም ለኪ |



## በቃል የሚጠና ጥቅስ

‹‹ ብዘገይ ግን፥ በእግዚአብሔር ማደርያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡››
(፩ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፲፭)

# ምዕራፍ ሁለት
# መታዘዝና ጥሩ ልጅ መሆን

## የምዕራፉ ዓላማ

ልጆች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ:

- የመታዘዝን መልካምነት ይረዳሉ።
- ምን አይነት ትእዛዝ መታዘዝ እንዳለባቸው ያውቃሉ።
- በመታዘዝ የሚገኘውን በረከት ያብራራሉ።

## ቁልፍ ቃላት

- መሥዋዕት፦ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ስጦታ ማለት ነው።
- በረከት፦ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ማለት ነው።

የማስጀመሪያ ጥያቄዎች:- ልጆች ስለ መታዘዝ ምን ታውቃላችሁ? ልጆች እናንተ ትታዘዛላችሁ ወይስ አትታዘዙም? ለማን ትታዘዛላችሁ? በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በታዛዠነታቸው ከሚታወቁ ልጆች የምታውቁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ::

- ልጆች መታዘዝ ማለት ኣድርግ የተባለውን ማድረግ እና አታድርግ የተባለውን ኣለማድረግ ማለት ነው::

## ፪.፩ ለሰው ሁሉ መታዘዝ

ልጆች የታዘዝነው ትእዛዝ ክፉ ሥራ ካልሆነ በስተቀር ሰዎች ሲያዙን መታዘዝ አለብን::

ለምሳሌ፦

- ቤተሰቦቻችን የሚያዙንን ትዕዛዝ መፈጸም ሲልኩን መላክ አለብን::
- አስተማሪዎቻችን የቤት ሥራ የክፍል ሥራ ሲሰጡን መሥራት አለብን፤
- ታላለቆቻችን ተው ሲሉን መስማት አለብን፤
- መምህራኖቻችን ዝም በሉ ሲሉን ዝም ማለት አለብን መረበሽ የለብንም::

👉ጓደኞቻችን ሰዎችን ተሳደቡ ወይም ከልጆች ጋር ተደባደቡ ቢሉን ማድረግ የለብንም፣

👉ጓደኞቻችን የራሳችን ያልሆነን ነገር ውሰዱ ቢሉን መታዘዝ የለብንም።

## ፪.፪ በመታዘዝ የሚገኝ በረከት

ልጆች የምንታዘዝ ከሆነ ፤

👉እግዚአብሔር ይባርከናል ፣

👉ዕድሜአችን ይረዝማል ፣

👉ወላጆቻችን ይመርቁናል ፣

👉ሰዎች ሁሉ ይወዱናል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ውስጥ በመታዘዝ ብዙ በረከት ያገኙ ቅዱሳን ሰዎችን ታሪክ አሁን እንማራለን።

## ታዛዡ ልጅ ይስሐቅ

👉ልጆች በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ትምህርታችሁ ስለ ይስሐቅ በሰፊው ትማራላችሁ፣

👉ይስሐቅ ለእናቱ ለሣራ እና ለአባቱ ለአብርሃም የሚታዘዝ ጥሩ ልጅ ነበር፣

👉ከመታዘዙ የተነሳ አባቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ፈተና እንዲያልፍ አድርጎታል፣

👉ታሪኩ እንዴት መሰላችሁ እግዚአብሔር አብርሃምን በጣም ይወደው ነበር አብርሃምም እግዚአብሔርን በጣም ይወደዋል።

- አብርሃም በጣም ደግ ሰው ነበር ። እግዚአብሔር አብርሃምን “ልጅህን ሰዋልኝ” አለው አብርሃምም በስተእርጅና የወለደውን አንድ ልጁን ሊሰዋ ታዘዘ።
- ‘ወደ ተራራ እንሂድ’ አለው ልጁ ይስሐቅም እሺ በማለት ወደ ተራራው አብረው ሄዱ። ታዲያ ከተራራው ግማሽ ላይ ሲደርሱ ይስሐቅ አባቱን ‘የመሥዋዕቱ በግ የታለ?”ብሎ ጠየቀ።
- አባቱም “እግዚአብሔር ያዘጋጃል” አለው ይስሐቅም እሺ ብሎ አብሮት ሄደ። ተራራው ጫፍ ሲደርሱ አባቱ ይስሐቅን “ዛሬ መሥዋዕት የምትሆነው አንተ ነህ።” አለው ይስሐቅም እሺ አለ።
- ይስሐቅ በጣም ወጣት እና ጠንካራ ነበር አባቱ አብርሃም ደግሞ መቶ አመት ያለፈው ሽማግሌ ነበር። ይስሐቅ እንቢ ማለት ይችላል። ገፍቶት መሮጥም ይችል ነበር። ነገር ግን ይስሐቅ ታዛዥ ስለነበር ሽማግሌው አባቱ እንደ በግ ሊያርደው እጅ እና እግሩን ሲያስረው ዝም ብሎ ታሰረ።
- በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የአብርሃምን መታዘዝ የይስሐቅንም ለአባቱ መታዘዝ ሲያይ አብርሃምን ተው አለው። “ልጅህን እንዳትሠዋ።” ብሎ የታሰረ ነጭ በግ ላከለት እና ያንን በግ በይስሐቅ ፈንታ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጎ አቀረበ።

## የዮሴፍ መታዘዝ

- ዮሴፍ ለእናት እና ለአባቱ ታዛዥ የሆነ ጥሩ ልጅ ነበር። አንድ ቀን አባቱ ያዕቆብ በእረኝነት እያገለገሉ ለነበሩት ወንድሞቹ ምግብ እንዲያደርስ አዘዘው።
- የዮሴፍ ወንድሞችም ሩቅ መንገድ ሄደው ስለነበር ዮሴፍ ሊያገኛቸው አልቻለም ወንድሞቹን ስላጣቸው ተስፋ ቆርጦ አልተመለሰም። አባቱ ያዘዘውን ለመፈጸም ብዙ ጥረት አድርጓል።
- በመጨረሻም የታዘዘውን በሚገባ ለመፈጸም ቻለ። አባቱ የላከውንም መልእክት አደረሰ ።
- ልጆች የታዘዛችሁትን ትዕዛዝ ለመፈጸም ምን ያህል ትተጋላችሁ? ዮሴፍ በመታዘዙ ምክንያት እግዚአብሔር ብዙ በጎ ነገር አድርጎለታል ። ክፉ ነገር ሲገጥመው እግዚአብሔር እረድቶታል። እስር ቤት ሲታሰር አስፈትቶታል። በግብጽ ሀገር ንጉሥ አድርጎ በክብር ሾሞታል?

## ፯.፬ ጥሩ ልጅ መሆን

- ልጆች ጥሩ ልጅ መሆን ማለት እንደ ይስሐቅ እና እንደ ዮሴፍ መታዘዝ፤ እግዚአብሔርን ማስደሰት ማለት ስለሆነ ብዙ በረከት (ሽልማት) አለው።

- ስለዚህ እናንተም እንደ ይስሐቅ እና እንደ ዮሴፍ ታዘዥና ጥሩ ልጅ ስትሆኑ እግዚአብሔር ብዙ ነገር ያደርግላችኋል። በትምህርታችሁ ጎበዝ እንድትሆኑ ትምህርታችሁን ይገልጽላችኋል። ሰዎች ሁሉ፤ እንዲሁም መምህራኖቻችሁ እንዲወዱአችሁ ያደርጋል። ሌላም ብዙ የምትፈልጉትን ነገር ያደርግላችኋል።

## ማጠቃለያ

ልጆች በዚህ ትምህርት "አባት እና እናትህን አክብር" የሚለው የእግዚአብሔር ሕግ ወላጅ አባትና እናታችንን ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት፣ በትምህርት በአጠቃላይ በሥጋና በመንፈስ የወለዱንን ሁሉ ማክበርና መንከባከብ እንደሚገባን በሚገባ አውቃችኋል። ስለዚህ እናንተም እግዚአብሔር በረጅም ዕድሜና ጤና እንዲባርካችሁ በሥጋና በመንፈስ የወለዱአችሁን፣ታላላቆቻችሁንና እርስ በርስ በመከባበር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፈጽሙ።

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

፩. ለማንኛዉም ሰው መታዘዝ በረከት ያስገኛል

፪. የማይታዘዙ ልጆች እረጅም ዕድሜ ይኖራቸዋል።

፫. ይስሐቅ ለወላጆቹ ታዛዥ ልጅ ነበረ።

በ "ሀ" ስር የተዘረዘሩትን በ "ለ" ስር ካሉት ጋር ተስማሚያቸውን በመስመር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩. ለመሥዋዕት የቀረበ ልጅ | ሀ. መስቀል |
| ፪. ለወንድሞቹ ምግብ ያደረሰ ልጅ | ለ. ይስሐቅ |
| ፫. በካህናት እጅ የምንሳለመው | ሐ. ዮሴፍ |



## በቃል የሚጠና ጥቅስ

‹‹እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ አባትህን እና እናትህን አክብር።››
(ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፳ ቁጥር ፲፪)

# ምዕራፍ ሦስት
# ጓደኝነት

## የምዕራፉ ዓላማ

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ፡-

- ጥሩ እና ጥሩ ያልሆነ ጓደኝነትን ይለያሉ።
- ሰውን ሁሉ ያለልዩነት ይወዳሉ።

## ቁልፍ ቃላት

ጓደኛ፡- መልካም ወዳጅ ማለት ነው።

የማስጀመሪያ ጥያቄዎች፡- ልጆችዬ ስለ ጓደኝነት ምን ታውቃላችሁ?
ልጆች እናንተ ጓደኛ አላችሁ? ጥሩ ጓደኛችሁ ማነው እናንተ ጥሩ ጓደኛ ናችሁ?
ሰውን ሁሉ ያለልዩነት መውደድ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኂል?

## ፫.፩ ሰውን ሁሉ ስለመውደድ

- ልጆች እኛ የክርስቶስ ተከታዮች ስለሆንን እሱ ያደረገውን ነገር ማድረግ አለብን፣
- ከእነዚህ በጣም መልካም ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ ሰውን ሁሉ መውደድ ነው፣
- ጌታችን ሁሉንም ሰው ይወዳል ፣ለሁሉም ሰው ሕይወቱን አሳልፎ ሰጥቷል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው የተሰቀለው ለሁሉም ሰው ነው:: (የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፲፮) ፣
- ልጆች ጌታችን ሰውን ሁሉ ይወዳል:: ሰዎች ኃጢአተኛ ቢሆኑ እንኳን ይወዳቸዋል ስለዚህ እኛም ሰዎችን ሁሉ መውደድ አለብን::




ሥዕል ፲.፩ ፡ የጌታችን ሥነ ስቅለት

## ፲.፪ ጥሩ ጓደኝነት

- ልጆችዬ ጓደኛ አላችሁ?
- እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ብቻውን እንዲኖር አይደለም አብሮት የሚኖር ረዳት እንዲኖረው አድርጎ ነው፡፡
- ነገር ግን ልጆች መልካምና መልካም ያልሆኑ ጓደኞችን መምረጥ አለብን፡፡

### የመልካም ጓደኝነት ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፡

- ቤተክርስቲያን እንድንሄድ ያደርጋል፣
- ለቤተሰቦቻችን እንድንታዘዝ ያደርጋል፣
- ትምህርታችንን እንድናጠና ያደርጋል፣
- እና ሌሎችንም በጎ ነገሮችን እንድናደርግ ያግዘናል፡፡

👉ልጆች እናንተም ለጓደኞቻችሁ መልካም ጓደኛ መሆን አለባችሁ። መልካም ከሆናችሁ እግዚአብሔር ይደሰትባችኋል።

## ፫.፫ መጥፎ ጓደኝነት

ልጆች መጥፎ ጓደኛ የመልካም ጓደኛ ተቃራኒ ነው። ክፉ ጓደኛ እግዚአብሔር አይደሰትበትም። መልካም ያልሆነ ጓደኛ የሚከተሉትን ያደርጋል።

👉ቤተክርስቲያን እንዳንሄድ ያደርጋል፣

👉ለቤተሰቦቻችን እንዳንታዘዝ ያደርጋል፣

👉ትምህርታችንን እንዳናጠና ያደርጋል፣

👉እና ሌሎችንም በጎ ነገሮችን እንዳናደርግ ያደርገናል፣

👉ትምህርቱን ስለማያጠና እኛም አናጠናም ካላጠናን ደግሞ ሰነፍ እንሆናለን። ሰነፍ ልጅ ደግሞ በእግዚአብሔርም በሰዎችም ፊት ክብር የለውም።

ልጆችዬ ይህንን የሚያደርጉ ልጆች ጓደኞቻችሁ ከሆኑ እንዲያቆሙ ንገሯቸው፤ እናንተም እንዲህ የምታደርጉ ከሆነ ማቆም አለባችሁ። ምክንያቱ ምን መሰላችሁ እንዲህ ባለ ሥራ እግዚአብሔር ደስ አይለውም። ክፉ ነገር ከሰይጣን ነው። እናንተ ደግሞ የእግዚአብሔር ስለሆናችሁ በጎ ነገር ብቻ ነው ማድረግ ያለባችሁ።

## ማጠቃለያ

ልጆችዬ ስለጥሩ ጓደኛም ይሁን ስለመጥፎ ጓደኝነት በተገቢው መንገድ ተምራችኋል፡፡ ሁልጊዜ መልካም ጓደኛ እንዲኖረን አስቀድመን የጓደኞቻችንን ማንነት እና ውሏቸውን በደንብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ምንም ብንዋደድ እንኳን መጥፎ የሚሠራ ጓደኛ ካለን መምከር እና ለቤተሰቦቹ መንገር የሚገባን ሲሆን ካልተለወጠ ደግሞ ከክፉ ጓደኛ መራቅ ያስፈልጋል፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

፩. ከሚከተሉት ውስጥ ጥሩ ጓደኝነትን የሚገልጸው የቱ ነው?

ሀ/ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ ይላል

ለ/ ለቤተሰቦቻችን እንድንታዘዝ ያደርጋል

ሐ/ ሁሉም መልስ ናቸው

፪. እኛ የክርስቶስ ተከታዮች ነን ስንል ምን ማለት ነው?

ሀ/ ሰውን ሁሉ እንወዳለን

ለ/ የሚወዱንን ለይተን እንወዳለን

ሐ/ የሚጠሉንን እንጠላለን

፫. ከሚከተሉት ውስጥ ጥሩ ያልሆነ ጓደኝነትን የሚገልጸው የቱ ነው?

ሀ/ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ ይላል

ለ/ ለቤተሰቦቻችን እንዳንታዘዝ ያደርጋል

ሐ/ እንድናጠና ያደርጋል



## በቃል የሚጠና ጥቅስ

‹‹ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።››
(፩ኛ ቆሮንቶስ ሰዎች ፲፭ ቍጥር ፴፫)

# ምዕራፍ አራት
# ጸሎት

## የምዕራፉ ዓላማ

- ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ
- በጸሎት ለአምላካቸው ምስጋና እና ልመናን ያቀርባሉ::
- የቤተ ክርስቲያንን ሥርአት ጠብቀው ይጸልያሉ
- ስለምን  እና ስለማን መጸለይ እንዳለባቸው ይማራሉ::
- ጸሎትን የት ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ::

## ቁልፍ ቃላት

- ጸሎት ፦ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ምስጋና ማለት ነው::
- ልመና፦ እግዚአብሔር እንዲሰጠን የምንፈልገው ነገር ማለት ነው::

የማስጀመሪያ ጥያቄዎች ፡- ልጆችዬ ጸሎት ማለት ምን ማለት ነው?
ጸሎት ታደርጋላችሁ? መቼ እና የት?
በቃላችሁ የምትችሉትን ጸሎት አጠገባችሁ ላሉ ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

## ፬.፩ ጸሎት ምንድነው?

👉ልጆችዬ ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው፡፡ በጸሎት ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን፣ የሚያስፈልገንን እንጠይቃለን፡፡ ልጆች ጸሎት እግዚአብሔርን ለማመስገን እንጸልያለን፡፡ እኛ ሰዎች የተፈጠርነው እግዚአብሔርን ለማመስገን ከዛም ያዘጋጀልንን ክብር እና ገነትን ወርሰን ከእሱ ጋር ለዘለዓለም ለመኖር ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ስለፈጠረን ፣ስለሚመግበን፣ እናት እና አባቶቻችንን ስለሰጠን፣ቤተ ክርስቲያንን ስለሰጠን፣ ጤናችንን ስለሰጠን፣ ሀገራችንን ሰላም ስላደረገል እና ስለ ሌሎች ብዙ ብዙ ምክንያች ማመስገን አለብን፡፡

👉ልጆች እናንተስ እግዚአብሔርን ስለምን (ምን ስላደረገላችሁ) ታመሰግኑታላችሁ? ስለሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን፡፡

## ፬.፪ እንዴት እንጸልይ

ልጆች አሁን ደግሞ ስንጸልይ እንዴት መጸለይ እንዳለብን እንማራለን፡፡

### ቀጥ ብሎ በእግር በመቆም

👉ልጆች ማንኛውም ክርስቲያን ሕጻንም ሆነ ትልቅ ሰው ጸሎት መጸለይ ያለበት ቆሞ ነው፡፡ ግን የታመሙ ወይም መቆም የማይችሉ ሰዎች ከሆኑ ቁጭ ብለው መጸለይ ይችላሉ፡፡ ልጆች የምንቆመው ለእግዚአብሔር ያለንን ክብር ለመግለጽ ነው ፡፡

### እጆቻችንን በመዘርጋት

👉ልጆች እጆቻችንን የምንዘረጋው አንደኛ ሁሉን መስጠት ከሚችለው እግዚአብሔር የጠየቅነውን ለመቀበል ነው ሁለተኛ ደግሞ እጃችንን ስንዘረጋ የመስቀል ቅርጽ ስለምንሰራ ሰይጣንን ለማሳፈር ነው፡፡

### ዓይኖቻችንን ወደ ሰማይ በማሳንት

👉ዓኖቻችንን ወደ ሰማይ ማድረግን የተማርነው ከጌታችን ነው "እርሱ በጸለየ ጊዜ ዐይኖቹን ወደሰማይ አንስቶ ነበረ" ፡፡ፊታችንን እና መላ ሰውነታችንን በመስቀል ምልክት በማማተብ እንጀምራለን፡፡

### ማማተብ

👉ተማሪዎች የጸሎት ሥርዓትን በተመለከተ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ትምህርት በስፋት ትማራላችሁ



ሥዕል ፬.፩ ፡ እጁን ዘርግቶ በሥርዓት የሚጸልይ ሕፃን

## ፬.፫ አባታችን ሆይ እና እመቤታችን ሆይ

- ልጆች አባታችን ሆይ የሚለውን ጸሎት ታውቁታላችሁ? እስኪ ሙሉውን በሉት?

### ጌታ ያስተማረው ጸሎት

- “አባታችን ሆይ” የሚለው ጸሎት የጌታ ጸሎት ይባላል ምክንያቱ ምን መሰላችሁ ? ይህንን ጸሎት ጌታ ነው ለሐዋርያት ያስተማራቸው:: (የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩ ከቁጥር ፩ እስከ ፫)

ልጆች አባታችን ሆይ በሚለው ጸሎት

- እግዚአብሔርን እናመሰግንበታለን ፤
- የዕለት ምግባችንን እንጠይቅበታለን፤

- 👉 እኛን ያስቀየሙንን ሰዎች ይቅር እንድንል ያስተምረናል፣
- 👉 ከክፉ ነገር እንዲጠብቀን እንጠይቅበታለን ፣
- 👉 እግዚአብሔር አባታችን እኛም ልጆቹ መሆናችንን የምናውቅበት ነው፡፡



ሥዕል ፬.፪ ፡ ምስለ ፍቁር ወልዳ

## የእመቤታችን ጸሎት

- 👉 በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ብሎ የሚጀምረው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት ነው፣
- 👉 እመቤታችን የጌታችን እናት ናት፣ የእኛም እናታችን ናት፣
- 👉 የዓለም ሁሉ እናት እና እመቤት ስለሆነች ለእሷ የሚገባትን ምስጋና እና በምልጃዋ ከልጇ እንድታማልደን በዚህ ጸሎት እንጠይቃለን፡፡


## ፬.፬ ስለምን እንደምንጸልይ

ልጆች ስንጸልይ ስለሚከተሉት ነገሮች መጸለይ እንችላለን

- ስለ ቤተክርስቲያን ስለ ሀገራችን
- ስለ ቤተሰባችን ስለ ራሳችን
- ስለ መምህራኖቻችን ስለ ታመሙ ሰዎች
- ስለተራቡ ሰዎች ስለታሰሩ ሰዎች
- ስለ ዓለም ሰላም ስለ እነዚህን ሁሉ መጸለይ አለብን፡፡

## ፬.፭ የት እንደምንጸልይ

ልጆች ጸሎት በሁሉም ቦታ መጸለይ እንችላለን፤ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ስለሚገኝ ፤ በጣም ተመራጭ የሆነው የጸሎት ቦታ ግን በቤተክርስቲያን ነው፡፡



ሥዕል ፬.፫ ፡ ምዕመናን በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ሲያደርጉ

# ማጠቃለያ

ልጆች ስለ ጸሎት ዛሬ ተምራችኋል ከዚህ በኋላ ጸሎት መጸለይ ግዴታችሁ ስለሆነ እንድትጸልዩ እሺ፡፡

## ማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡

፩. ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው

፪. ተኝተን መጸለይ አንችላለን፡፡

፫. በሁሉም ቦታ ላይ መጸለይ እንችላለን፡፡



## በቃል የሚጠና ጥቅስ

‹‹አቤቱ ፥ ጸሎቴን ስማኝ፥ የአፌንም ቃል አድምጥ፡፡››

(መዝሙረ ዳዊት መዝሙር ፻፵ ቍጥር ፪)

# ምዕራፍ አምስት
## መዝሙር

### የምዕራፉ ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ

- መዝሙር የመዘመርን ጥቅም ይረዳሉ
- እንዴት መዘመር እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡

### ቁልፍ ቃላት

ዜማ፦ በመዝሙር የሚቀርብ ምስጋና

👉 መዝሙር ልዩ ልዩ ቃና ባለው ድምጽ በዜማ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ምስጋና ነው፡፡

## ፳.፩ የመዝሙር ጥቅም

### ፩. እግዚአብሔርን በተመስጦ ለማመስገን

👉ልጆች ሰዎች ከልባቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና ሲያቀርቡ በተመስጦ ዘመሩ ይባላል ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን ያስደስተዋል፡፡ ምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ በወህኒ ቤት የዘመሩት መዝሙር፡፡

### ፪. ወደ እግዚአብሔር ልባዊ ጸሎት ለማቅረብ

👉መዝሙር ጸሎታችንንም በዜማ ማቅረብ እንድንችል ያደርጋል፡፡ አባታችን ቅዱስ ያሬድ ጸሎቱን ያቀርብ የነበረው በጣፋጭ ዜማ ነው፡፡

### ፫. ለሕይወታችን / ለነፍሳችን ጥቅም

👉ነፍሳችንን ለማስደሰት ፣ እንደ ቅዱስ ዳዊት ርኩስ መንፈስንም ለማባረር መዝሙር ይጠቅማል ፡፡ (፩ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ አስራ ስድስት ቍጥር ሃያ ሦስት)

## ፳.፪ መዝሙር ስለመዘመር

ልጆች መዝሙር መዘመር ለእግዚአብሔር መስዋእት ማቅረብ ስለሆነ በሥርዓት እና በአግባቡ መሆን አለበት፡፡

መዝሙር መዘመር ልክ እንደ መላእክት ያለ ዕረፍትና ያለ ድካም ለመዘመር የሚያስችል ጸጋ የሚያሰጥ ነውና ልንወደው ይገባል፡፡

## ፰.፫ እንዴት እንዘምር?

👉 ልጆች አሁን ደግሞ እንዴት መዘመር እንዳለብን እንማራለን፡፡

### ፩ አለባበስ

👉ልጆች ለመዝሙር የተለየ አለባበስ አለው ፡፡ ይህ የአለባበስ ሥርዓት የተወሰደው ከመላእክት ነው፡፡ (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፮ ከቁጥር ፩ እስከ ፬) መላእክት ሲዘምሩ ሥርዓት ባለው በከፍተኛ ድምፅ ነው ፤ ለዚህ ነው እኛም ድምፃችንን ከፍ አድርገን ማመስገን ያለብን፡፡

### ፪ በሥርዓት መመራት

ቤተክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ አባቶቻችን በአስቀመጡላት ሥርዓት የምትመራ ናት፡፡ ከአባቶቻችን የተቀበልነውን እኛም በሥርዓት መያዝ እና ለታናናሾቻችን ማስተላለፍ አለብን፡፡ (፪ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፮)

ስለዚህ ልጆች እግዚአብሔር በሚወደው በአባቶቻችን ሥርዓት ሆነን በሽበሽባ እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን፡፡ (መጽሐፈ ነህምያ ፲፪፡ ፳፯ ፤፪ኛ ዜና መዋልዕ ምዕራፍ ፯ ቁጥር ፮)

## ማጠቃለያ

ልጆች ዛሬ ስለ መዝሙር ተማርን እንዴት መዘመር እንዳለብንም የአባቶቻችንን ስርዓት ጠብቀን መዘመር እንዳለብንም ተማርን አይደል? ስለዚህ መዝሙር ትልቅ ጸጋ እንደሆነ እና እግዚአብሔርንም እንደሚያስደስተው አውቀን በሥርዓት መዘመር አለብን ማለት ነው፡፡ የአባቶቻችን የቅዱስ ዳዊትና የቅዱስ ያሬድን ጸጋና በረከት ያሳድርብን አሜን፡፡

### የቃላት ጨዋታ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅ | ዱ | ስ | ያ | ሬ | ድ | ሽ | ቅ | በ | ማ |
| ዱ | ዱ | መ | ዝ | ሙ | ር | ብ | ዱ | ረ | ስ |
| ስ | ል | ስ | መ | ማ | ወ | ሽ | ስ | ከ | ተ |
| ዳ | ባ | መ | ጳ | ተ | ሬ | ባ | ሲ | ት | ላ |
| ዊ | ዊ | ዘ | ዝ | ው | ማ | ሰ | ላ | መ | ለ |
| ት | ጸ | መ | ያ | ጸ | ሎ | ው | ስ | ቀ | ፍ |
| ነ | ሎ | ር | ሬ | ጋ | ጸ | ስ | የ | በ | የ |
| ፍ | ት | አ | ለ | ባ | በ | ስ | ኛ | ል | ገ |
| ስ | በ | ተ | መ | ስ | ጦ | መ | ዘ | መ | ር |
| የ | አ | ባ | ቶ | ቻ | ስ | ር | ዓ | ት | ነ |



# በቃል የሚጠና ጥቅስ

## ‹‹ለእግዚአብሔር ዘምሩ እግዚአብሔርንም አመስግኑ፡፡››

## (ትንቢተ ኤርሚያስ ምዕራፍ ፳ ቁጥር ፲፫)